# ”ሆድ ሲያውቅ…”

**ረዲ ከአራዳ**

መድረክ አሁን ላይ በአባላቱ አዲስ የነውጥ ስልት በአገር ውስጥና በውጭ ሚዲያዎች ስሙ ተደጋግሞ ከመነሳቱ ውጭ የፈጠረው አዲስ የፖለቲካ አስተሳሰብም ይሁን የተረጋጋ ፖለቲካ እንዲኖር እያደረገ ያለው ምንም አይነት እንቅስቃሴ የለም፡፡ በእርግጥ አዲስ ሊባል የሚችለው የሰማይና የምድርን ያህል ርቀት ያላቸው አስተሳሰብ ባለቤት የሆኑ አባላት ማሰባሰቡ ነው ፡፡እነዚህ ሃይሎችም ከዚህ በፊት በተናጠል ሲተገብሩት የነበረውን አፍራሽ ፖለቲካዊ ተግባራቸውን አጠናክረው ለመቀጠል በማሰብ የተለያዩ ፓርቲዎችና ግለሰቦች ስብስብን አቀናጅቶ አመራሮቹን ይፋ ማድረጉ ነው ፡፡

በቅድሚያ የወቅቱ የመድረኩ ሊቀመንበር ተደርገው የተቀመጡትን ዶ/ር  መራራ ጉዲናን  እንኳን ብናይ ከዚህ በፊት ከነበራቸው የግለሰቡ ባህሪና ፖለቲካዊ ፍላጐት አንፃር ተነስተን የቀጣይ የመድረኩን አላማ ምን እንደሆነ መረዳት እንችላለን፡፡ ግለሰቡን ከዚህ በፊት የምናውቃቸው ለአገር ጥቅም በመቆርቆር በሚያነሱት አማራጭ የመፍትሄ ሃሳብ ሳይሆን በአገሪቱ ላይ ያልተረጋጋ ፖለቲካዊ ሁኔታ እንዲፈጠር ለማድረግ በፅያፍና ባልተገራ ግርድፍ አነጋገራቸው በሚሰነዝሩት አሉታዊ አስተያዬታቸው ነው፡፡ እንዲያውም ከዚህ ንግግራቸው አንዳንዶቻችን የተገነዘብነው ሰውየው አላቸው ከሚባለው የትምህርት ደረጃና ወክየዋለሁ ከሚሉት የህብረተሰብ ክፍል የሞራል እሴት በተቃረነ መልኩ ከተናገሩ በኋላ ማሰብ የሚጀምር መሆናቸውን ነው ፡፡

በተለያየ ወቅት ሰውየው የሚያነሱት ሀሳቦች በአገራችን ያልተረጋጋ የፖለቲካ ሁኔታ የመፍጠር ፣ህብረተሰቡ ከረጅም ጊዜ የትግል ውጤት በኋላ ያገኘውን ሰላም፣ ዴሞክራሲ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት አደጋ ላይ የመጣልና ሁከትና አመፅን የማራገብ አላማ ያላቸው ናቸው ፡፡ ይህን ደግሞ ማንም መስካሪ ሳያሻን በአንድ ወቅት በአንድ የግል ጋዜጣ ላይ ግለሰቡ እራሳቸው በምርጫ 97 ሲከተሉት

የነበረውነ ፀረ ህገ - መንግስታዊ እንቅስቃሴ በአንደበታቸው መመስከር መቻላቸውን መጥቀስ ይቻላል፡፡ በአጠቃላይ ሰውየው አላማቸው ይችን አገር በበጎ ለመለወጥ ሳይሆን ከዚህ በፊት ሳይወራረድ የቀረ የደም መፈሰስና የእርስ በእርስ መተላለቅ እውን ለማድረግ ማለም ብቻ ነው፡፡ በዚህም ባህሪያቸው በአሁኑ ወቅት ድምፁን ሰጥቶ የመረጣቸው የአካባቢያቸው ህዝብ እንኳን በሰውየው ድርጊትና ሁኔታ እያፈረባቸው መሆኑን ለመግለፅ ተገዷል፡፡

እንግዲህ እነዚህ ሁሉ የሰውየው እውነታዎች ናቸው ከህብረተሰቡ ጋር ሊያቆራርጧቸው የቻሉት፡፡ በሌላ በኩል ካለው እውነታ በመነሳት ዶክተር መራራ መድረክ በተባለው ፓርቲ ወስጥ ምንም ሊያስመርጥ የሚችል ጥንካሬ ሳይኖራቸው የስብሰቡ ሊቀመንበር ተደርገው መመረጣቸው ከዚህ ቀደሙ በሚያራምዱት የነውጥ አቋም ክፉኛ የተለከፉ የፓርቲው አባላት መበራከታቸውን የሚያሳይ ነው ፡፡ይህም መድረኩ ተመሳሳይ አላማን ወደፊትም በተጠናከረ አኳኋን ለመቀጠል ያሰበ መሆኑ በግልፅ ለማሳየት ያስችላል፡፡

መድረክ የአገራችንን ዴሞክራሲያዊ ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ለማስቀጠል የተዘጋጀ ስበስብ ቢሆን ኖሮ ሊከተለው የሚገባው መስመር በተግባር እየታየ ካለው የተለየ መሆን ይገባዋል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የመድረክ ስብስብ ለህዝብ ግልፅ ተደርጐ ሊቀርብለት ይገባል፡፡ በተቃራኒው ግን ምርጫ 2002 እየቀረበ ባለበት በምርጫ ታሳቢ የተፈጠረው መድረክ በብዙ ጉዳዬች ላይ ለማንም ግልፅ ባልሆነ መልኩ የትርምስና የግርግር መናኸሪያ መሆን ጀምሯል፡፡ የህዝብ ውክልና ሊሸከም የተዘጋጀ የፖለቲካ አደረጃጀት መሆኑ ቀርቆ በአገራችን ህዝብ ላይ የዘመተ የጠላት ኃይል ወደ መምሰል እየተሸጋገረ መጥቷል፡፡ ለዚህ ማሳያ የሚሆነው የመድረኩ ሊቀመንበር ከአንድ የተቃዋሚ ሬዲዮ ጣቢያ ጋር ያደረጉትን ቃለ ምልልስ ብንመለከት እንደ አመራርነታቸውና የስብስባቸውን አዲስነት አስመልክቶ ለህዝቡ ብዙ ማለትና ማሳወቅ ሲገባቸው እንዲያው የተለመደውን የሰውየውን የዘወትር የስድብና የዘለፋ ንግግር ብቻ ነው ልናደምጥ የቻልነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ጠያቂው የሚፈልገውን እንዲናገሩና የራሱን ተልእኮ ለመወጣት ያደረገው ሙከራ በዶ/ር መራራ ላይ ሙሉ በሙሉ ተሳክቶለት በሚፈልገው መልኩ ተጠቅሞባቸው

አልፏል፡፡ ይህ የሚያሳየው ደግሞ ሰውየው የህዝብና የአገር ጉዳይ እንደማያስጨንቃቸውና በተገኘ አጋጣሚ ሁሉ የአፍራሽነት ተልእኮን ለመተግበር መዘጋጀታቸውን ነው፡፡

ዶ/ር መራራ ጉዲናን በምንም ጉዳይ ላይ በድፍረት ከመናገር እንደማይቦዝኑ በመረዳት መድረክ መሪው አድርጐ መርጧቸዋል፡፡ በድፍረት የመናገራቸው ሚስጥር የሰውየው የማስተዋል ችሎታቸው ሳይሆን ከግል ጥቅምና ስልጣን ባሻገር የአገር ጉዳይ በእሳቸው ዘንድ የተሰጠው ቦታ እንደሌለ ከራሳቸው አንደበት ልንረዳ እንችላለን፡፡ ለምሳሌ በአንድ ወቅት በሪፖርተር ጋዜጣ ላይ ምርጫ 97ን አስመልክቶ ህገ ወጥ መንገድን መከተላቸውን በድፍረት ለህዝብ ይፋ አድርገዋል፡፡ ይህን አፍራሽ መንገድ መከተላቸው ሳያሳፍራቸው በየሚድያው በልበ ሙሉነት እየገለፁት መገኘታቸው በተቃራኒው በሰላም ወዳዱ የኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ ትዝብት ላይ ጥሏቸዋል ፡፡ በዚህ መልኩ የምናውቃቸውን ግለሰብ ነው እንግዲህ መድረክ መሪው አድርጐ የመረጣቸው፡፡

በእርግጥ ሰውየውን በትክክል ከተረዳናቸው ያሏቸው የባህሪ መገለጫዎች በቀጣይ በአገራችን ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ውስጥ ተቀባይነት የሌላቸው ናቸው፡፡ በተቃራኒው ይህ ባህሪይ ግን የአመፅና የጥፋት መንገድን መከተል ለፈለገ አፍራሽ ኃይል ተመራጭ ሆኖ ተገኝቷል ፡፡ ለዚህ አፍራሽ ተግባራቸው ደግሞ መድረክም ሊቀመንበሩ አድርጎ በመምረጥ ሰውየውን እየተጠቀመባቸው ነው፡፡ በዚህም የመድረክን የአመራር አባላት አሰላለፍ ተገንዝቦ ስለመድረክ ቀጣይ ጉዞ መገመት ነብይ መሆንን የማይጠይቅ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

የስምንት ፓርቲዎችና የሁለት ግለሰቦች ስብስብ መሆኑ የሚነገርለት መድረክም ይሁን በተናጠል ፓርቲዎቹ የሚከተሉት የፖለቲካ ፍልስፍና ለህዝብ ግልፅ ካለመሆኑ በተጨማሪ የአመራሮቻቸው ግራ የሚያጋባና የተዘበራረቀ አቋም ተደማምሮ ግልፅነት የተፈጠረበት ሁኔታ የለም ፡፡ ይልቁንም የመድረክ መቋቋም እስካሁን የነበረውን የአገራችንን የፖለቲካ ስነ ምህዳር እንዳሰፋው አመራሮቻቸው

በድፍረት የሚናገሩበትንና ለራሳቸው የሚሰጡትን ምስክርነት ትተን ዳኝነቱን ለህዝብ ከተውነው እውነታው ሌላ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

በቀጣዩ ምርጫ ስነ - ምግባር ደንብ ላይ እየተደረገ ያለው ውይይት ከመድረክ ውጭ በሰላም እየተከናወነ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በሌላ በኩል መድረክ በዚህ ውይይት ላለመሳተፍ መወሰኑ በቀጣይም ቢሆን ምርጫውን በሰላም እንዲካሄድ የራሱን እገዛ ላለማድረግ መወሰኑን የሚያሳይ ነው፡፡

መድረክ የትኛውንም ይሁን የተሻለ የፖለቲካ አስተሳሰብ ያራምድ በዚህች አገር እስካለ ድረስ ወደ ስልጣን ሊመጣ የሚችለው በሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ ምርጫ መሳተፍ ሲችል ብቻ ነው፡፡ መድረክ በምርጫ አሸናፊ ለመሆን የተሰባሰበ መሆኑን እየገለፀ ባለበት ሁኔታ መጪው  ምርጫ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ለማድረግ በሚካሄድ ውይይት ላይ ረግጦ መውጣቱና ላለመሳተፍ መወሰኑ  ለአገራችን የዴሞክራሲ ሂደት መጕልበት ያለውን ንቀት ያሳያል፡፡በሰላማዊ መንገድ በሚካሄድ ምርጫ በሚገኝ ውጤትም ላለመገዛት መፈለጉን ያሳያል፡፡

የመድረክና የአባል ፓርቲዎች ድራማ በዚህ ብቻ የሚያበቃ አይደለም፡፡ መድረክ በምርጫ ስነ ምግባር ደንብ ላይ ላለመሳተፍ አቋም ቢወስድም በተናጠል በውስጡ ያሉ ፓርቲዎች ወደ ድርድር ለመምጣት መሞከራቸው የመድረክን ያልጠራ መስመር በግልፅ ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል እንዲሁ በፓርቲዎች መካከለ የሚደረገውን የጋራ ድርድር ባልተሳተፉበት ሁኔታ የቀጣዩን ምርጫ አስመልክቶ በመድረክ ውስጥ የታቀፉ አንዳንድ ፓርቲዎተ ከደጋፊዎቻቸው ጋር እያደረጉ ያሉት ውይይት ሊታይ የሚገባው በበጐ ነው፡፡ ነገር ግን ምርጫው ሰላማዊ እንዲሆን ለማስቻል ከደጋፊዎቻቸው ጋር ያደረጉትን ውይይት ከሌሎች ፓርቲዎች ጋር ለማድረግ አለመፍቀዳቸው በአገሪቱ ላይ ተቋማዊ አሰራሮች ተዘርግተው የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዳያበረክቱና ሌሎች ህገ ወጥ መንገዶች እንዲከፈቱ ካላቸው ፍላጐት ጋር የሚያያዝ ነው፡፡

የተለያየ አሰላለፍን ተግባራዊ በማድረግ እየተገበሩ ያሉት ግራ የማጋባት አካሔድ በህዝቡ ዘንድ ሊፈጥር የሚችለው ብዥታ ለአገር የማይጠቅም ነው፡፡ ቀጣዩን ምርጫ ሰላማዊ ለማድረግ በጋራ እንደ ፓርቲ እንዲደራደሩ ሲጠየቁ በራቸውን ዝግ ማድረጋቸው ሊታይ የሚገባው ምርጫውን ሰላማዊ እንዳይሆን ለማድረግ ከማሰብ አንፃር ነው፡፡ ይህን እያደረጉ ባሉበት ሁኔታ ከደጋፊዎቻቸው ጋር ምርጫውን አስመልክቶ አያደረጉ ያሉት ውይይትም ለጥፋታቸው ማስተባበያ እንዲረዳቸውና ርካሽ የህዝብ ተወዳጅነትን ለማግኘት ሲባል ነው፡፡ ለምሳሌ ዶ/ር መራራ ጉዲና ከተናገሩት ብንነሳ ‹‹ መንግስት እኔን ቢያስር የሚከተለውን ያውቃል›› ብለው መናገራቸው ህዝብን ለምን አላማ ለማነሳሳት በማቀድ መሆኑን በግልፅ ያሳየናል፡፡”ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ” እንዲሉ ይህ ንግግር ሰውየው ከተናገሩ በሁዋላ የሚያስቡ በመሆናቸው የአመፅና የሁከት ቀስቃሽ ንግግራቸው የህግ ተጠያቂነትን ያመጣብኛል ከሚል ፍርሃት ጋር ይያያዝ ይሆናል እንጂ የህዝብ ድጋፍ እንኳን እንደሌላቸው ጠንቅቀው ያውቁታል ፡፡

በመጨረሻ ለማጠቃለል እንዲረዳኝ ማንሳት የምፈልገው ከምርጫ 97 ጋር ተያይዘው የተነሱ ጉዳዮችን ነው፡፡ ምርጫ 97 ለአገራችን የዴሞክራሲ ሂደት አዲስ ምእራፍ ከፋች መሆኑን አሳይቶን አልፏል፡፡ ህዝቡ ከዚያ ብዙ ትምህርት የወሰደበትም አጋጣሚ ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ መላው ህዝብ በምርጫ ተሳታፊ የሆነበት ሁኔታ የሚያሳየው ህዝቡ ለአገሩ ለውጥ ምን ያህል ኃላፊነት የሚሰማው እንደሆነ ያሳየ ሲሆን በተቃራኒው ከምርጫው ማግስት በጥፋት ኃይሎች ጠንሳሽነት በተቀሰቀሰ ህገ ወጥ እንቅስቃሴ ያለ አግባብ የተከፈለው መሰዋእትነት ለህዝቡ አስተምሮ ያለፈው ትምህርት ቀጣይ ከተመሳሳይ ስህተት እንዲቆጠብ አድርጎታል፡፡ ስለዚህ በአገራችን ተቀባይነት ሊኖረው የሚችለው አካሄድ በሰላማዊ መንገድ የሚደረግ የምርጫ ሂደት እንጂ በአቋራጭ ወደ ስልጣን የሚያወጣ የአመፅ መንገድ ዝግ ከመሆኑም በተጨማሪ እስከ መጨረሻው ከህዝብ የሚያቆራርጥ ተግባርም ጭምር ይሆናል፡፡